# ወረርሽኝ EBT (P-EBT): (P-EBT): የት/ቤቶች አስቸኳይ የምግብ መርሀግብር
# በተደጋጋሚ የሚነሱ ጥያቄዎች

1. **P-EBT፣ ወይም የወረርሽኝ EBT የትምህርት ቤቶች አስቸኳይ የምግብ መርሀግብር ምንድን ነው?**
   በኮቪድ-19 ምክንያት፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ነጻ ወይም በቅናሽ ዋጋ ምግብ ማግኘት የሚገባቸው ልጆች ተጨማሪ የምግብ ጥቅማጥቅሞችን ያገኛሉ። P-EBT ትምህርት ቤትዮች ተዘግተው የነበሩ በመሆናቸው ምክንያት፣ ቤተሰቦች የምግብ ሸቀጣሸቀጦችን መግዛት እንዲችሉ ለመርዳት ትብሎ የተቀየሰ አዲስ እና ጊዜያዊ የምግብ ጥቅማጥቅም/ድጎማ ነው።

2. **P-EBT ማግኜት የሚችለው ማን ነው?**
   ነጻ ወይም የቅናሽ ዋጋ ምግቦችን የማግኜት አግባብነት ያላቸው ከK-12ኛ ክፍል ድረስ ያሉ ተማሪዎች ቤተሰቦች ሁሉ - ይህም ምግብ *ለሁሉም* ተማሪዎች ነጻ ከሆነበት ት/ቤት ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎችን ይጨምራል።

   የዜግነት ወይም የስደተኝነት ሁኔታዎቻቸው ምንም ይሁን ምን፣ P-EBT ለሁሉም ተማሪዎች ነው። ብቸኛው መስፈርት፣ አንድ ልጅ (ተማሪ) ለነጻ ወይም ለቅናሽ ዋጋ የት/ቤት ምግቦች አግባብነት ወይም ብቃት ያለው መሆን ነው።

3. **ልጄ ብቁ ከሆነ/ች፣ ምን ያክል ገንዘብ አገኛለሁ?**
   የሚያገኙት ገንዘብ መጠን በቤተሰብዎ ውስጥ ነጻ ወይም ቅናሽ ዋጋ የት/ቤት ምግቦች የሚቀበሉ ልጆች ብዛት/ቁጥር ላይ የተመሰረተ ነው። ከፍተኛው ጥቅም በልጅ $399 ነው። ለሁሉም ልጆችዎ አንድ የP- EBT ካርድ ያገኛሉ (ለምሳሌ፡ 3 ልጆች ካሉዎት፣ አንድ ካርድ ከ$1,197 ጋር ያገኛሉ)።

   ለነጻ እና ቅናሽ ዋጋ ምግቦች ብቁነታቸውን ት/ቤታቸው ከተዘጋ **በኋላ** ያገኙ ልጆች ቤተሰቦች፣ በያንዳንዱ ልጅ ከ$399 **የሚያንስ** ያገኛሉ። ዋናው ነገር፣ ቤተሰብዎ ለነጻ እና ቅናሽ ዋጋ ምግቦች፣ ወይም ለመሰረታዊ ምግብ ያመለከተበት ጊዜ ላይ የተመሰረተ ይሆናል። የP- EBT ጥቅማጥቅሞች (ማለትም፣ በቀን $5.70) ት/ቤቶች ተዘግተው በቆዩባቸው የትምህርት ቀናት ቁጥር ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡

   ማርች - $68.40
   አፕሪል - $125.40
   ሜይ - $119.70
   ጁን - $85.50

4. **P-EBT በኔ ወይም በቤተሰቤ የስደተኝነት ሁኔታ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል ወይ? P-EBT የሚያገለግለው ለU.S. ዜጎች ብቻ ነው እንዴ?**
   አይደለም። P-EBT በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ ለአገልግሎቱ ብቁ ለሆኑ ልጆች ሁሉ ነው፣ የነሱ ወይም የወላጆቻቸው የስደተኝነት ሁኔታን ግምት ውስጥ የማያስገባ ነው። ለ P-EBT ሲያመለክቱ፣ ስለእርስዎም ሆነ ስለልጅዎ የስደተኝነት ወይም የዜግነት ሁኔታ አይጠዬቁም። P-EBT በህዝብ ቁጥጥር (ፓብሊክ ቻርጅ) ስር የሚካተተ **አይደለም።** (ለመበለጠ መረጃ **ጥያቄ #17ን** ይመልከቱ)።

5. **ልጆቼ እንዴት P-EBT ያገኛሉ?**

P-EBT ለማግኘት ሁለት መንገዶች አሉ:

**መሰረታዊ የምግብ** (የምግብ ማህተም) **ላላቸው ቤተሰቦች**: በጁን 28ኛ እና ጁላይ 7ኛ ቀናት መካከል ባሉት ወቅት፣ የP- EBT ጥቅማጥቅሞች አሁን እዬተጠቀሙበት ካለው EBT ካርድዎ ላይ ይጨመራሉ።

**ነጻ ወይም ባለቅናሽ ዋጋ የት/ቤት ምግቦችን የሚቀበሉ ልጆች ቤተሰቦች**: ከኦገስት 31፣ 2020 በፊት ወይም በአዲስ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ (ከኋለኛው በአንዱ) ላይ አንድ ቀላል ማመልከቻ መሙላት ይኖርብዎታል።

6. **ለ P-EBT እንዴት ነው የማመለከተው?**

ለማመልከት ሁለት መገዶች አሉ:

1. **በመስመር ላይ:** www.WashingtonConnection.org (በማመልከቻው ላይ፣ በምግብ እርዳታ ክፍል ውስጥ) 'Pandemic EBT - Emergency School Meals Program' የሚለውን ሳጥን ይምረጡ።



**ወይም፣**

2. **ይደውሉ:** 877-501-2233 (DSHS ለደንበኞች አገልግሎት የግንኙነት ማዕከል። የቋንቋ ትርጉም አገልግሎት አለ)

ለማመልከት፣ ስለ እያንዳንዱ ልጅ ማወቅ የሚገባዎት:

- የልጅዎ ት/ቤት ስም ወይም ት/ቤቱ የሚገኝበት ክልላዊ መስተዳድር
- የልጅዎ የመጀመሪያ እና መጨረሻ ስም ልክ በት/ቤት የምዝገባ ሬኮርድ ላይ ሰፍሮ እንድደሚገኘው
- የልጅ የልደት ቀን

**የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ተቀባይነት የሚያገኙት፣ ለት/ቤት የምግብ ማመልከቻ ላይ የቀረበው የልጅዎ ዝርዝር መረጃ ለ P-EBT በቀረበው ማመልከቻ ላይ ከቀረበው መረጃ ጋር የሚጣጣም ከሆነ ነው።**

የ EBT ካርድዎ የት እንደሚላከልዎ በ P-EBT ማመከቻዎ ላይ መምረጥ ይችላሉ። ልጅዎ (ልጆችዎ) ተቀባይነት ካገኙ፣ የ EBT ካርድዎ ከቅባሎቱ 3-5 ቀናት በኋላ ባሉት ጊዚያት ውስጥ በፖስታ ይደርስዎታል።

በማመልከቻዎች የስራ መደራረብ ምክንያት፣ ማመልከቻዎን መርምሮ ለማስተናገድ እስከ 30 የስራ ቀናት ሊወስድ ይችላል።




7. **ለ P-EBT ለማመልከት የመጨረሻው ቀነገደብ መቼ ነው?**

   እስከ ከኦገስት 31፣ 2020 ወይም ከአዲስ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ቀደም ብለው (ከኋለኛው በአንዱ) ወቅት ማመልከት ይኖርብዎታል።

8. **ተቀባይነት አግኝቼ እንደሆነ እንዴት አውቃለሁ?**

   የEB ካርድዎን እንዴት እንደሚጠቀሙ የሚገልጽ መረጃ የያዘ የEB ካርድ በኢ-ሜል ይደርስዎታል። (እንዴት ማመልከት እንደሚቻል የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ ቁጥር 6 ላይ ይመልከቱ)። ለነጻ እና ቅናሽ ዋጋ የት/ቤት ምግቦች ተቀባይነት ያገኙት ት/ቤቶች ከተዘጉ በኋላ ከሆነ፣ የማጽደቅ ሂደቱ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችላል።

   የ P-EBT ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ፣ ምን እንደተፈጠረ እና ውድቅ መደረጉም አግባብ አይደለም ብለው የሚያምኑ ከሁኑ እንዴት ይግባኝ እንደሚሉ የሚገልጽ ደብዳቤ በፖስታ ይደርስዎታል።

9. **የ P-EBT ካርድ በፖስታ ሲደርሰኝ ምን ማድረግ አለብኝ?**

   ከ “EBT” ካርድዎ ጋር የሚመጡትን መመሪያዎች ይከተሉ። ምግብን ከመግዛትዎ በፊት ካርድዎን ማግበር አለብዎት። ካርድዎን ለማግበር፣ ደውለው በ P-EBT ማመልከቻዎ ላይ የሰፈረውን የዚፕ ኮድለየመልእክት አድራሻዎ ይሰጣሉ። ከዚያም ወደ ግብይት በሚሄዱበት ጊዜ የሚጠቀሙበትን የግል ፒን ቁጥርዎን ይፈጥራሉ - ልክ እንደ ዴቢት ካርድ።

10. **የEBT ካርዳችን ከተሳሳተ የገንዘብ መጠን ጋር ቢደርሰንስ?**

    መጠኑ ትክክል አይደለም ብለው ካሙኑ፣ ለ DSHS የደንበኞች አገልግሎት የግንኙነት ማዕከል ይደውሉ በ 877-501-2233 ይደውሉ።

11. **P-EBT ካገኘን በኋላም፣ ልጆች ከት/ቤቶች እና ሌሎች ድርጅቶች አሁንም ምግብ ማግኘት ይችላሉ?**

    አዎ። ልጆች ምግብ ከት/ቤቶች ማግኘት እና P-EBT ማግኘት ይችላሉ። እነዚህ የተለያዩ መሀግብሮች ናቸው። የP-EBT ጥቅማጥቅሞች ከት/ ቤት ወይም ከሌሎች ድርጅቶች ምግብ ማግኘትን አይተኩም።

12. **የ P-EBT ጥቅማጥቅሞችን ስንት ጊዜ አገኛለሁ?**

አንድ ጊዜ። P-EBT እንደ የምግብ ማህተም ወይም እንደ WIC ወርሃዊ ድጎማ አይደለም።

13. **በመስመር ላይ አመልክቼ የ P-EBT ካርዴን ያላገኘሁ፣ ወይም ማመልከቻዬን ውድቅ የሚያድደርግ ደብዳቤ ከደረሰኝስ?**

ለማህበረሰባዊ እና ጤና አገልግሎቶች ክፍል (DSHS) የደንበኞች አገልግሎት
የግንኙነት ማዕከል በስልክ ቁጥር:  877-501-2233 ይደውሉ።
ክፍት የሚሁበት ወቅቶች: **8am - 5pm, ከሰኞ እስከ ዓርብ** (ከህዝብ በዓላት ውጪ)

14. **በ P-EBT ድጎማዎች ምን መግዛት እችላለሁ?**

P-EBT ከማንኛውም የSNAP - ተቀባይነት ካለው መደብር፡ በርካታ የምግብ ሸቀጥ መደብሮች፣ የገበሬዎች ገበያዎች፣ አንዳንድ የመንገድ ዳር ትናንሽ ሱቆች፣ ውስጥ ምግብ መግዛት ይችላል፣ ወይም (እንደሚኖሩበት አካባቢ)፣ እንደ አማዞን እና ወልማርት ከመሳሰሉ የመስመር ላይ (አንላይን) መደብሮች ምግብ መግዛት ይቻላል።
P-EBT የሚከተሉትን ነገሮች ለመግዛት <u>አያገለግልም</u>:

- ምግብ ያልሆኑ ነገሮች (ለምሳሌ: ለጽዳት የሚሆኑ ነገሮች፣ የሽንት ጨርቆች፣ የሴቶች ንጽህና መጠበቂያ፣ ወዘተ)
- አልኮል መጠጥ
- ትኩስ ወይም የተዘጋጁ ምግቦች (ለምሳሌ: ደሊ ምግቦች፣ የዶሮ ጥብስ፣ ወዘተ)
- ቫይታሚኖች ወይም ሚኔራሎች

የ EBT ካርድዎን እንደ ዴቢት ካርድ ይጠቀሙ:

- "EBT"ን ይምረጡ
- የEBT ካርድዎን ስዋይፐ ያድርጉ
- የግል ፒን ቁትርዎን (PIN) ያስገቡ

15. **ካርዴን ስቀበል የ P-EBT ጥቅሜን ሁሉ መጠቀም አለብኝ?**

የለም። የ P-EBT ጥቅም የሚኖርዎት ካርድዎን ከተቀበሉ በኋላ ላለው ለአንድ ዓመት ነው።

16. **ጥያቄዎች ካሉኝ ለማን ነው የምደውለ?**

ለ 877-501-2233 (DSHS' የደንበኞች አገልግሎት የግንኙነት ማዕከል ይደውሉ)
8am - 5pm፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ (ከኅዝብ በዓላት ውጪ)

17. **ስለ P-EBT እና ለአረንጓዴ ካርድ/ህጋዊ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ ማመልከት ስለመቻሌ ጥያቄዎች ቢኖሩኝስ?**

ለ P-EBT ማመልከት ወይም P-EBTን መጠቀም ለአረንጓዴ ካርድ (ለህጋዊ ቋሚ የመኖሪያ ፈቃድ) ማመልከት በምቻልዎ ላይ ምንም ተጽዕኖ **<u>አይኖረውም</u>**። ለ P-EBT ማመልከት እዚህ በዩናይተድ ስቴትስ ውስጥ የሚኖርም ሆነ ወይም ከ U.S. ውጪ የሚኖር የቤተሰብ አባልን ለአረንጓዴው ካርድ ለማመልከት ያለው ችሎታ ላይ ተጽዕኖ **<u>አይኖረውም</u>**። P-EBT በህዝብ ቁጥጥር (ፓብሊክ ቻርጅ) ውሳኔ ስር የሚወድቅ **<u>አይደለም።</u>** ስለስደተኝነት ሁኔታዎ እና ስለ P-EBT ጥያቄዎች ካሉዎት፣ የስደተኛ ጉዳዮች የህግ ባለሙያ ወይም በ DOJ የተረጋገጠ ዕውቅና ያለው ወኪል ወይም ነገረፈጅ ማነጋገር አለብዎት ሰሜናዊ ምዕራብ የስደት-ገብ መብቶች ፕሮጀችት (Northwest Immigrant Rights Project (NWIRP)) ስለ P-EBT እና ስለስደት ህጎች ያውቃሉ፤ ስለሆነም፣ ጥያቄዎችዎን ሊመልሱልዎት ይችላሉ፡

- <u>NWIRP Seattle Office</u>: 206-587-4009

- NWIRP Yakima Valley (Granger) Office: 509-854-2100
- NWIRP Wenatchee Office: 509-570-0054
- NWIRP Tacoma South Office: 206-816-3893

18. ***መሰረታዊ ምግብ ወይም ነጻ ወይም ቅናሽ የት/ቤት ምግቦች የማያገኙ ዝቅተኛ ገቢ ያልቸው ቤተሰቦች እንዴይ የ P-EBT ጥቅም/ድጎማ ማግኘት ይችላሉ?***

ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች ያሏቸው ሆነው፣ ነገርግን አሁን በቅርቡ ስራቸውን ወይም ገቢያቸውን ያጡ ቤተሰቦች፣ ከጁን 30፣ 2020 **በፊት** እና ለ P-EBT ከማመልከታችሁ **በፊት** በትምህርት ቤቶቻችሁ ክልላዊ መስተዳድር በኩል ለነጻ እና ቅናሽ የት/ቤት ምግብ ማመልከት ትችላላችሁ። እንደዚሁም ደግሞ፣ ከጁን 30፣ 2020 በፊት ለመሰረታዊ ምግቦች በመስመር ላይ (ኦንላይን) (www.WashingtonConnection.org) ማመልከት ትችላላችሁ፣ ወይም በስልክ ቁጥር (877-501-2233 – DSHS ለደንበኞች አገልግሎት ማዕከል) መደወል ትችላላችሁ። ለመሰረታዊ ምግብ ብቁ ሆናችሁ ከተገኛችሁ፣ እንደዚሁም ዕድሜያቸው ለምህርት ለደረሱ ልጆቻችሁ የP-EBT ጥቅማጥቅሞችንም ታገኛላችሁ።

.

ለመሰረታዊ ምግብ ወይም ለነጻ ወይም ቅናሽ የት/ቤት ምግብ ተቀባይነት ያገኛችሁት ት/ቤቶች ከተዘጉ *በኋላ*፣ እና ከጁን 30፣ 2020 *በፊት* ከሆነ፣ የ P-EBT ጥቅማጥቅሞች በዬደረጃው ተመጥኖ-እዲሰራጭ ይደረጋል።

USDA Nondiscrimination Statement

*This institution is an equal opportunity provider.*